MOST

የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር

# በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሽግግርና ምርምር የላቁ የማምረቻ ተቋማትና ተመራማሪዎች የሽልማት መመሪያ

**569/2013**

አዲስ አበባ

ሚያዝያ 2008 ዓ.ም

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርእስ

ይህ መመሪያ "የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሽግግርና ምርምር የላቁ የማምረቻ ተቋማትና ተመራማሪዎች የሽልማት መመሪያ ቁጥር 569 / 2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

1 "ሳይንስ" ማለት ነባራዊውን አለም እና የተፈጥሮ ህግጋትንና ክስተቶችን ለማብራራትና ለመገንዘብ የሚያስችለንን እውቀት በምልከታና በሙከራ የምናገኝበት ዘዴ ነው፡፡

2 "ቴክኖሎጂ" ማለት የአንድን ህብረተሰብ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመፍታትና የኑሮ ደረጃውን ለማሻሻል የሚያስችል፣ የምርት አመራረትና የአገልግሎት አሰጣጥ፣ ከአጠቃቀም ጋር የተጣመረ ዕውቀት፣ የድርጊት ጥበብ (Knowhow)፣ የአሠራር ዘዴና ሥርዓት ነው፡፡

3 "የፈጠራ ስራ" ማለት የተፈጠረ ቴክኖሎጂን የሚያሻሽል፣ ለነበረ ቴክኖሎጂ አዲስ የጥሬ ዕቃ ምንጭ ወይም አዲስ ገበያ የማስገኘት ወይም በነበረ ቴክኖሎጂ ላይ በማከል ቴክኖሎጂውን የተሻሻለ፣ የቀለጠፈ ወይም በዚሁ የማሻሻል ሥራ የተነሳ የማምረቻ ወይም የአገልግሎት ጊዜንና ወጪን የሚቀንስ ወይም ገበያን የሚያሰፋ ቴክኒካዊ የመፍትሄ ሃሳብ ነው፡፡

4 "ቴክኖሎጂ ሽግግር" ማለት በሌሎች ወገኖች የተፈጠረና በተግባር የተፈተነ ቴክኖሎጂን ወይም የአሰራር ዘዴን በካፒታልና በኢንተርሚዲየር ዕቃዎች ወይም በሰለጠነ የሰው ኃይል ወይም በቴክኒክና ንግድ መረጃዎች አማካኝነት ወደ ተቀባይ ወገኖች የማስተላለፍ ሂደት ሆኖ፣ ይህ ሂደት የተሟላ የሚሆነው ከሰጪው/ ከአቅራቢው የተላለፈው ዕውቀት ተቀባዩን ተመሳሳይ ምርት ለማምረትና አገልግሎት ለመስጠት ሲያስችለው ነው፡፡

5 "ምርምር" ማለት በሳይንስና ቴክኖሎጂ መስኮች የሚካሄድ ችግር ፈቺና ተግባራዊ የሚደረግ አዲስ ግኝት ወይም ማሻሻያ ነው፡፡

6 "ተመራማሪ" ማለት በሳይንስና ተክኖሎጂ ዘርፍ በተናጠል ወይም በቡድን የአንድን ችግር መፍትሄ ለማግኘት በተደራጀና ሳይንሳዊ ዘዴ በመከተል የሚካሄድ የምርምር ስራን የሚያከናውን ግለሰብ/ቡድን ነው፡፡

7 "ተግባራዊ ምርምር" ማለት አንድን ነባራዊ ችግር ለመቅረፍና አዲስ ዕውቀት ለማግኘት የሚካሄድ ምርምር ዘዴ ነው፡፡

8 "የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ሀገራዊ የትኩረት አቅጣጫዎች" ማለት ለሀገር እድገት የላቀ አስተዋፅዖ አላቸው ተብለው በመንግስት ቅድሚያ የተሰጣቸው ዘርፎች ሲሆኑ ጨርቃ ጨርቅ፣ ብረታ ብረት፣ ቆዳና የቆዳ ውጤቶች፣ ኬሚካል ምግብ መጠጥ እና መድሀኒት፣ አግሮ ፕሮሰሲንግ፣ ባዮ-ቴክኖሎጂ፣ ኢንፎርሜሽን እና ኤሌክትሮኒክስ፣ ኮንስትራክሽን፣ ማዕድን፣ ኢነርጂ፣ ውሀ፣ ግብርና ፣ ናኖ ቴክኖሎጂ፣ ማቴሪያልስ ሳይንስ፣ ህዋ ሳይንስ እና የጤናው መስክ ናቸው፡፡

9 "የምርምር ሥነ ምግባር ጥሰት" ማለት ትክክለኛና ሞራላዊ ያልሆነ እና የተሟላ የምርምር ሂደት ሳይከተል በተለያዩ መንገዶች ማለትም አስመስሎ በማቅረብ እና በሌሎች ህገ ወጥ መንገዶች የተሰራ የምርምር ሂደት ነው፡፡

10 "ተቋማት" ማለት ዩኒቨርስቲዎች፣ የምርምር ማዕከላት፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና፣ ህጋዊ ማህበራት፣ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ የማምረቻ ወይም የኢንዱስትሪዎች የወል ስም ነው፡፡

11 "ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡

12 "አዲስ" ማለት አዲስ የደንበኛን ወይም የተገልጋይን ፍላጎትን የሚጋብዝ ወይም የሚስብ አዲስ የአመራረት ዘይቤ/መንገድ ወይም አዲስ ምርት፣ስርዓት ወይም የአመራረት ሂደት የፈጠራ ሀሳብ ነው፡፡

13 "የምርምር ቡድን " ማለት በአንድ የምርምር ስራ ላይ ሁለትና ከሁለት በላይ የሆኑ ባለሙያዎች በጋራ ለመስራት የፈጠሩት ስብስብ ነው፡፡

14 "የምርት ወይም የአገልግሎት ብዜት"ማለት አንድን የአገልግሎት ወይም የምርት ፈጠራ ግኝት በሌሎች መሰል ተቋማት በአነስተኛ ወጪ፣ ጊዜ እና ከፍተኛ ጥራት ተግባራዊ ማድረግ የሚቻል ሲሆን ነው፡፡

15 "የሽልማት ገምጋሚ ኮሚቴ"ማለት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚሰየሙ የሽልማት ገምጋሚ ኮሚቴዎች ሲሆኑ ሀላፊነታቸውም የዕጩ ተሸላሚዎችን/ተወዳዳሪዎችን ስራ መገምገም እና ውጤታቸውን ለሚኒስቴር መስሪያቤቱ ማሳወቅ ነው፡፡

16 "ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ" ማለት በሽልማት ግምገማ ወቅት የሚነሱ ቅሬታዎችን የሚመለከት፣ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አማካኝነት የሚቋቋም ሲሆን ኮሚቴውም ቅሬታውን በመፈተሽ የውሳኔ ሀሳብ የሚያቀርብ ነው፡፡

17 በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር ሴትንም ያካትታል፡፡

## 3. ዓላማ

ይህ መመሪያ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፤

1. ቅድሚያ ትኩረት በተሰጣቸው ሀገራዊችግር ፈቺ የምርምር ስራዎች ላይ የላቀ የምርምር ስራ በመስራት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ላደረጉ ተቋማት ዕውቅና እና ማበረታቻ ሽልማት ለመስጠት፤
2. የሳይንስና ቴክኖሎጂ የፈጠራ ዝንባሌ በህብረተሰብ ውስጥ ለማስረፅና ለማሳደግ ምቹ መደላድልና ተጨባጭ ሀገራዊ ንቅናቄ ለመፍጠር፤
3. የማምረቻና የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት በፈጠራ በታገዘ መልኩ የተሟላ ብቃታቸውን ተጠቅመው ለሚያመርቱት ምርት እና የተሻለ ተቋማዊ አደረጃጀትና ተያይዞ ለሚመጣ ውጤት ዕውቅና መስጠትና ለማበረታታት፣
4. ሀገራዊ የኢንዱስትሪ፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሽግግሩን ለማፋጠን በከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት፣ በምርምር ተቋማት፣ በማምረቻ ተቋማት ቴክኖሎጂን የመማር የመጠቀም እና የማሻሻል አቅም እንዲጎለብት በማድረግ የቴክኖሎጂ ሽግግሩን እንዲፋጠን ለማድረግ፤
5. የምርምርና ቴክኖሎጂን የመማር፣ የመጠቀም እና የማሻሻል አቅም እንዲጎለብት በማድረግ የኢንዱስትሪ እድገት ማፋጠን፤

## 4. የመመሪያው ተፈጻሚነት

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙና የኢትዮጵያ ዜግነት ያላቸው የማምረቻ፣ የከፍተኛ ትምህርት እና የምርምር ተቋማት የምርት ሂደትን በማሻሻል የሚቀርቡ፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር እና የምርምር ስራዎች በሚያከናውኑ ተቋማትና ተመራማሪዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል 2

## የሽልማት ምድቦች፣ ተወዳዳሪዎች ማሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች እና መምረጫ መስፈርቶች

### 5. የሽልማት ምድቦች

በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሽግግር የላቁ የማምረቻ ተቋማትና ተመራማሪዎችን ለማበረታታት የሚሰጠው ሽልማት ከዚህ በታች የተመለከቱት የሽልማት ምድቦች ይኖሩታል፤

1) ቴክኖሎጂን ያሸጋገሩ የማምረቻ ተቋማት ምድብ፡ እና
2) ችግር ፈቺ የምርምር ስራዎች ያከናወኑ ተመራማሪዎች ምድብ ናቸው፡፡

### 6. ተወዳዳሪዎች ማሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

#### 6.1. ችግር ፈቺ የምርምር ስራዎች ያከናወኑ ተመራማሪዎች ማሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

1. በዚህ መመሪያ መሰረት ለሽልማት የሚቀርቡ እጩ ተወዳዳሪዎች በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ወይም ምርምር ማዕከል ውስጥ የሚሰሩ ወይም በግል ምርምር የሚሰሩ ኢትዮጵያውያን ሆነው ከዚህ በፊት በማንም ያልተሰራ ወይም አዳዲስ ወይም ተጨባጭ ለውጥ ያለው ቴክኖሎጂያዊ የምርምር ሀሳብ ያቀረቡ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
2. የተካሄደው ችግር ፈቺ ምርምር ለህብረተሰቡ ተደራሽ ሆኖ ውጤት ያመጣ መሆን ይኖርበታል፡፡
3. ተወዳዳሪዎች ለውድድር የሚያቀርቧቸው የምርምርና የቴክኖሎጂ ሽግግር ስራዎች ልዩነት እስካላቸው ድረስ ከአንድ በላይ ስራዎችን አቅርበው መወዳደር ይችላሉ፡፡
4. የምርምር ስራው በተቋም ደረጃ የተሰራ ከሆነ ከተቋሙ የድጋፍ ደብዳቤ መቅረብ ይኖርበታል፡፡
5. በግል ለሚቀርቡ ችግር ፈቺ የምርምር ስራዎች የስራው የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት /utility model/ የተሰጣቸው መሆኑን የሚገልፅ መረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
6. ተወዳዳሪዎች ለዚህ ውድድር የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ ሙሉ በሙሉ ሞልተው ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

6.2. የላቁ ቴክኖሎጂዎችን ያሸጋገሩ የማምረቻ ተቋማት ማሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

1. በዚህ መመሪያ መሰረት ለሽልማት የሚቀርቡ እጩ ተወዳዳሪ ተቋማት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚሰሩና ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያላቸው አምራች ኢንዱስትሪዎች መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
2. በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ቴክኖሎጂን በመቅዳት/ በማላመድ ወይም የተወሰነ ማሻሻያ በማድረግ የምርታማነትና የአሰራር ሂደታቸውን ያዘመኑ ተቋማት መሆን አለባቸው፡፡
3. የቴክኖሎጂ ትግበራ ስራውን ተግባራዊ በማድረግ ለተጠቃሚው ተደራሽ ስለመሆኑ የሚያሳይ የድጋፍ ደብዳቤ ኢትዮጵያዊ ከሆነ ተጠቃሚ/ ተቋም ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
4. ስራው በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነትን ያተረፈና ኢኮኖሚያዊ አዋጭነቱ የተገጋገጠ መሆን ይኖርበታል፡፡
5. ከዚህ ቀደም የተሸለመ ተቋም በቀጣይ ውድድር ይዞ የሚቀርበው ስራ ቀደም ብሎ ሽልማት ካገኘበት ስራ የተለየ እስከ ሆነ ድረስ ከአንድ በላይ ስራዎችን አቅርቦ መወዳደር ይችላል፡፡
6. የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ሚዛንን የማያዛባና የአካባቢ ብክለት የማያስከትል መሆኑን ማሳየት የሚችሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
7. ተወዳዳሪዎች ከተቋማቸው እና ከቴክኖሎጂው ተጠቃሚዎች ስለአገልግሎቱ ጠቀሜታ ሊገልፅ የሚችል የድጋፍ ማስረጃ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
8. ተወዳዳሪዎች ለዚህ ውድድር የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ ሙሉ በሙሉ ሞልተው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፤

## 7. የመምረጫ መስፈርቶች

ለእያንዳንዱ የሽልማት ምድብ የመምረጫ መስፈርቶች ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው አባሪ 1 እና 2 መሰረት ይሆናል፡፡

## 8. ለተወዳዳሪዎች የሚሰጥ ሽልማት

አሸናፊ ተወዳዳሪዎች፡-

1. በየደረጃው የዕውቅና የምስክር ወረቀት፣
2. ሜዳሊያ (የነሃስ፣ የብር እና የወርቅ) እና
3. የገንዘብ ማበረታቻዎች ያገኛሉ፤

4. ከተሸላሚዎች መካከል እንደአስፈላጊነቱ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የአጭር ጊዜ የአቅም ማጎልበቻ ስልጠናዎች የሚያገኙበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

## ክፍል ሶስት

## የሽልማት ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ

9. **የሽልማት ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ ስለማቋቋም**

በሀገር አቀፍ ደረጃ በተወዳዳሪዎች የተሰሩ የምርምርና የቴክኖሎጂ ሽግግር ስራዎች ግምገማና መረጣን የሚያከናውን ሀገር አቀፍ የሽልማት ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ ይቋቋማል፤

1. ኮሚቴው የሽልማት ዘርፎቹን ባማከለ መልኩ ከተለያዩ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ተቋማት፣ ከሚመለከታቸው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች፣ ኤጀንሲዎችና ሌሎች ተቋማት የተውጣጡ ሆነው በዘርፉ ዕውቀትና ልምድ ያላቸውን ባለሙያዎችን የያዘ ሲሆን ከሙያው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ግለሰቦች ዕጩ ተወዳዳሪዎችን በአግባቡ ለመለየትና ለመምረጥ ኮሚቴውን የሚያግዙ ይሆናል፡፡
2. የኮሚቴው ሊቀመንበር እና እንደ አስፈላጊነቱም ምክትል ሊቀመንበር ከኮሚቴው አባላት ውስጥ የሚመረጡ ይሆናል፡፡
3. የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ተወካይ የኮሚቴው ፀሀፊ ይሆናል፡፡

10. **ሀገር አቀፍ የሽልማት ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ ተግባር እና ኃላፊነት**

1. በሁሉም የሽልማት ምድቦች የቀረቡ ተወዳዳሪዎችን ሰነድ እና ውጤት ትክክለኛነትና ህጋዊነት ያረጋግጣል፤
2. በተወዳዳሪዎች የቀረቡትን ስራዎችን በጥልቀት በማየት በተሰጠው መስፈርት መሰረት ይገመግማል፤ የማለፊያ ነጥብ በማስቀመጥ ለሽልማት ብቁ የሆኑትን በደረጃ ለይቶ ያቀርባል፤
3. በተወዳዳሪዎች የተሰሩ ስራዎችን በመስፈርቶቹ መሰረት በመገምገም በሀገር አቀፍ ደረጃ ውጤት ይሰጣል፤
4. የተመረጡትን እጩ ተሸላሚዎችን ጠቅላላ የአመራረጥ ሂደትና ውጤት ሪፖርት ለሚኒስቴሩ የበላይ አመራር በማቅረብ ያፀድቃል፡፡
5. ኮሚቴው ለወደፊቱ የሽልማት መመሪያው እንዲከለስ የማሻሻያ ሀሳብ/ግብዓት ለሚኒስቴር መስሪያቤቱ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

11. የሚኒስቴሩ ተግባርና ሃላፊነት

1. በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሚደረገው ሽልማት በጀት ያስመድባል፤
2. ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የፌደራልና የክልል የመንግስትና የግል ተቋማት ጋር በቅንጅት የሚሰራባቸው ምህዳር ይፈጥራል፤
3. ለተወዳዳሪዎች በሚኒስቴር መ/ቤቱ ድረ-ገፅ እና በተለያዩ ሚዲያዎች አማካኝነት የተሳትፎ ጥሪ ያቀርባል፤
4. ለውድድር የተዘጋጁትን መመሪያዎች፣ መስፈርቶችና ማስታወቂያዎች ተደራሽ እንዲሆኑ የመረጃ ዳሰሳ ያካሂዳል፤
5. በተወዳዳሪዎች የሚቀርቡ መረጃዎችን በማደራጀት ለብሄራዊ ገምጋሚ ኮሚቴ ያቀርባል፤
6. በየደረጃው የሚካሄደውን የሽልማት አፈፃፀም ክትትል ያደርጋል፤
7. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ያቋቁማል አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤
8. በገምጋሚ ኮሚቴ ተገምግሞ የቀረበውን የእጩ ተሸላሚዎችን መረጃ አግባብነት በማረጋገጥ ያፀድቃል፤
9. የተሸላሚዎችን መረጃ ያደራጃል፣ ያሰራጫል፡፡
10. የሽልማት ውድድሩን ሂደትና ውጤት በአህዝቦት ስራዎች በማስደገፍ ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆን ይሰራል፤
11. የላቀ ውጤት ላስመዘገቡት ተሸላሚዎች የማበረታቻ ሽልማት ይሰጣል፤
12. እንደአስፈላጊነቱ ለተሸላሚዎች የስራ ፈጠራና የአቅም ግንባታ የአጭር ጊዜ ስልጠና እና የገበያ ትስስር የሚፈጠርበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

12. የኮሚቴ የግምገማና መረጣ ጊዜ

ኮሚቴው የተወዳዳሪዎችን ስራዎች ለመገምገምና የመጨረሻውን ውጤት ለማሳወቅ የሚስፈልገውን ጊዜ በተመለከተ ሚኒስቴር መ/ቤቱና ኮሚቴው በሚያካሂዱት የጋራ ውይይት የሚወሰን ይሆናል፡፡

## ክፍል አራት

## <u>የማመልከቻ አቀራረብና የተሸላሚዎች አመራረጥ ሂደት፣ የቅሬታ አፈታት ስርዓት</u>

13. የማመልከቻ አቀራረብ

1. ተወዳዳሪዎች የምርምር፣ የምርት እና የአገልግሎት ስራዎቻቸውን ለውድድር እንዲያቀርቡ በተለያዩ መገናኛ ብዙሀኖች ማስታወቂያ የሚነገር ሲሆን በተጨማሪም በተመረጡ ቦታዎች ማስታወቂያ እንዲለጠፍ ይደረጋል፤

2. በሚኒስቴር መስሪያቤቱ ለአመልካቾች የማመልከቻ ቅፁን/ፎርሙን አሞላል እና ተያያዥ መረጃዎች በተመለከተ ከላይ በተጠቀሱት መገናኛ ብዙኃን እንዲገለፅ ይደረጋል፤
3. አመልካቹ አስረጂ የተሟላ የድጋፍ ሰነዶችን ከተጠቃሚውና ከተቋሙ ማቅረብ ይኖርበታል፤
4. ማመልከቻ የማቅረቢያ ጊዜ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚወሰን ሆኖ አመልካቾች በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ አስፈላጊ መረጃዎችን አሟልተው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

14. አመልካቾች ከውድድር ውጭ ስለሚሆኑበት አግባብ

1. አመልካቹ አስፈላጊና ደጋፊ መረጃዎችን በወቅቱ አሟልቶ ማቅረብ ካልቻለ፣
2. ከመመሪያው መስፈርት ውጭ የሆኑ ማመልከቻዎች ካቀረበ እና
3. ከዚህ በፊት በተደረጉ ተመሳሳይ የውድድር ሽልማቶች ላይ ከቀረቡና በተመሳሳይ ስራዎች ተሸላሚ ከሆኑ ከውድድር ውጭ ይደረጋሉ፡፡

15. የተሸላሚዎች አመራረጥ ሂደት

1. ተወዳዳሪዎች ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለዚህ ውድድር ያዘጋጀውን ማመልከቻ ቅጽ በአግባቡ ሞልተው እንዲሁም የስራዎችን ዝርዝር መግለጫና ማብራሪያ የያዘ ፕሮፖዛል እና ተያያዥ ደጋፊ ሰነዶችን በማያያዝ ይመዘገባሉ፤
2. ሚኒስቴር መ/ቤቱም የቀረቡ ተወዳዳሪዎችን ስራዎችንና ሰነዶችን በማደራጀት ቅድመ-ማጣራት በማድረግ ለተቋቋመው ሀገር አቀፍ ገምጋሚ ኮሚቴ ያቀርባል፤
3. ኮሚቴው በሚኒስቴሩ ተዘጋጅተው በሚቀርቡለት የሽልማት መመሪያ መስፈርቶች መሰረት የቀረቡትን የተወዳዳሪዎች ማስረጃና ሰነዶችን በጥልቀት ይገመግማል፤
4. ኮሚቴው አባሪ በተደረገው የነጥብ መስጫ ቅጽ መሰረት ለሀገር አቀፍ ሽልማት ብቁ የሆኑትን ተወዳዳሪዎች ነጥብ በመስጠትና ስራዎቻቸውን በአካል እንዲያቀርቡና እንዲያስረዱ በማድረግ በደረጃ በመለየት መርጦ ለሚኒስቴሩ ለውሳኔ ያቀርባል፤
5. የተመረጡ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በሚኒስቴሩ የበላይ አመራር ይሁንታን አግኝቶ ሲጸድቅ የተሸላሚዎች ውጤት ይፋ ይደረጋል፡፡

16. የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ስርዓት

ተወዳሪዎች ወይም ተሸላሚዎች ወይም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት በሽልማት አመራረጥ ሂደት፣ የተለያዩ አገልግሎቶች እና አሰራሮች ላይ ቅሬታ ካላቸው በሚኒስቴሩ የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ስነስርዓት መሰረት የሚፈታ ይሆናል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

17. መመሪያውን ስለማሻሻል

ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው መመሪያውን ሊያሻሽል ይችላል፡፡

18. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በሚኒስትሩ ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ሚያዝያ ........................................ ቀን 2008 ዓ.ም

አብይ አህመድ

ሚኒስትር

አብይ አህመድ
ሚኒስትር

19. አባሪዎች

አባሪ 1

1. ችግር ፈቺ የምርምር ስራዎች ለመሸለም የመምረጫ መስፈርቶች

1.1 የምርምር ስራው ማጠቃለያ፡-

1.1.1 የምርምር ሃሳቡ መነሻ

1.1.2 ምርምሩን ለመስራት የተጠቀመበት ስልት

1.1.3 የምርምሩ ወሰን

1.1.4 ከዚህ ምርምር የተገኘ ዕውቀት

1.1.5 ከዚህ ምርምር የተገኘ ጥቅም

1.1.6 ምርምሩ ቀድሞ ከነበረው በቴክኖሎጂ ዕድገት ያለው ለውጥ

2 የምርምር ግኝቱ/ውጤቱ መገለጫ

| ተ.ቁ | የመገምገሚያ መስፈርቶች | ክብደት በፐርሰንት | የተሰጠው ዋጋ |
|---|---|---|---|
| 1. | የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተፈፃሚነት መንግስት ቅድሚያ ትኩረት በሰጣቸው ዘርፎች ችግር ፈች የምርምር ግኝቶች ያመጣው ውጤት<br>• ምርታማነትን ከማሻሻል ወይም/እና<br>• አገልግሎት አሰጣጥን ከማዘመን ወይም/እና<br>• የገቢ ምርቶች በመተካት እና የውጭ ንግድ በማሳደግ | 30 | |
| 2. | የምርምር ግኝቱ ልዩ ባህሪይ<br>• በዋጋ ተመጣጣኝነት<br>• በቀላሉ ተግባራዊ ከመሆን አንፃር<br>• ወጪ ቆጣቢ መሆኑ<br>• ጥራቱን የጠበቀ መሆኑ<br>• የምርት አመራረት ሂደት/ቅደም ተከተል የሚያሳይ ሰነድ መኖሩ | 20<br>4444<br>4 | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 3. | የምርምር ግኝቱ አስተዋፅዖ<br>• የተፈጥሮ ሀብትን በአግባቡ ከመጠቀም አንፃር<br>• በባህላዊ መንገድ የምንጠቀምባቸው ቴክኖሎጂዎችን ከማዘመን አኳያ<br>• የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕውቀቶችን ከማስተላለፍ አንፃር<br>• የህብረተሰቡን በተለይም የሴቶችን የስራ ጫና የሚቀንስ ስለመሆኑ<br>• የአካል ጉዳተኞችን መሰናክሎች/ ተግዳሮቶች የሚቀርፍ ስለመሆኑ | 20 | |
| 4. | የምርምር ግኝቱ የስርጭት ሽፋን<br>• ሀገር አቀፍ<br>• በተወሰነ አካባቢ/ኢንዱስትሪ/ ተቋም ወይም ሌሎች | 18<br>18<br>12 | |
| 5. | የምርምር ግኝቱ አስተማማኝነት እና በቀላሉ የመባዛት ሁኔታ<br>• የምርምር ግኝቱ በተቋምም ሆነ በግለሰብ ደረጃ ወደ ገቢ ማስገኛ የመቀየር ብቃት<br>• የአገልግሎቱ አስተማማኝነትና የአገልግሎት ዕድሜ | 12<br>6<br>6 | |

አባሪ 2

የማምረቻ ተቋማት የሽልማት መስፈርቶች

ከዚህ በታች በተመላከተው ዝርዝር መስፈርት ውጤታማ የውጭ ቴክኖሎጂዎችን በማስገባትና በመጠቀም የምርትና የምርታማነት ደረጃ ያሻሻሉ የማምረቻ ተቋማት መገምገሚያ መስፈርት ነው፡፡

| ተ.ቁ | የመገምገሚያ መስፈርቶች | ክብደት በፐርሰንት | የተሰጠው ዋጋ |
|---|---|---|---|
| 1. | የቴክኖሎጂ ሽግግሩ ያመጣው ተጨባጭ ለውጥ እና ጥቅም<br>1.1ከማህበራዊ ጉዳዮች አንፃር<br>• የህብረተሰቡን የአኗኗር ዘይቤ (ትምህርት፣ ጤና፣ የሚያሻሽል ስለመሆኑ)<br>• ለህብረተሰቡ ባህል፣ የስራ ተነሳሽነት፣ ጤና፣ ትምህርት እና ሌላ መሻሻል የጎላ አስተዋፅዖ የሚያበረክት ስለመሆኑ<br>• ለሴቶች እና አካል ጉዳተኞች ምቹ ሁኔታ የመፍጠር አቅሙ<br>• ህብረተሰቡ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ውጤቶች ያለው ግንዛቤ እንዲዳብር የማድረግ አቅሙ | 10 | |
| | 1.2ከኢኮኖሚ ጉዳዮች አንፃር<br>• ገቢ የማስገኛ አቅም በማዳበር እና አላስፈላጊ ወጪዎች በመቀነስ ያለው ፋይዳ<br>• የገቢ ምርቶች በመተካት እና የውጭ ንግድ በማሳደግ ያበረከተው አስተዋፀዖ<br>• የስራ እድል የመፍጠር አቅሙ<br>• የምርትን ጥራት፣ ዋጋ እና በቴክኖሎጂ ምጥቀት ተወዳዳሪነትን የሚያሳድግ ስለመሆኑ | 10 | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | 1.3ከአካባቢ ልማትና ጥበቃ አንፃር<br>• የተፈጥሮ ሀብትን ያለ ብክለት ከመጠቀምና ከማልማት አኳያ ያለው ፋይዳ<br>• አግባብነት ያለው አላስፈላጊ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን የማስወገጃ ሂደት ያለው ስለመሆኑ | 10 | |
| 2. | 1.1የቴክኖሎጂ አቅም<br>• ቴክኖሎጂውን የማግኘት፣ የመረዳት እና በሙሉ አቅም የመጠቀም ብቃት<br>• በምርት ወይም በአሰራር ሂደት ተግባራዊ የተደረገው ቴክኖሎጂ በራስ አቅም የመዘርጋት እና የማሻሻል አቅም ስለመኖሩ<br>• ቀጣይነት ባለው መልኩ በገበያ ተወዳዳሪ ለመሆን መሰናክሎችን በመቅረፍ የቴክኖሎጂውን ምርታማነት እንዲያድግ /update የማድረግ አቅም ስለመኖሩ | 20 | |
| 3. | የጋራ ተጠቃሚነትን ከማስፋት አንፃር ያለው ትስስር<br>• ከአነስተኛ፣ መካከለኛ እና ከከፍተኛ ኢንዱስትሪዎችጋር ያለው የሁለትዮሽ ትስስርን በማጠናከር ውጤታማ እንዲሆን አስቻይ ሁኔታዎችን የፈጠረ ስለመሆኑ<br>• የቴክኖሎጂ ሽግግሩ የጎንዮሽ እንዲስፋፋ ተሞክሮዎችን ቀምሮ ከማስፋት አንፃር የተሄደ ርቀት<br>• ቴክኖሎጂን በመቀበልም ሆነ በማስተላለፍ ላይ መሰረት አድርጎ የደረሰ ስምምነት joint venture ስለመኖሩ እና ያስገኘው ፋይዳ<br>• ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ ከምርምር ማዕከላት እና ቴ/ሙ/ት/ስ ኮሌጆች ጋር በጋር የመስራት ሁኔታ ስለመኖሩ | 15 | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 4. | ጥራት ያለው የስራ አመራር በኢንዱስትሪው/በአምራች ተቋሙ ስለመኖሩ<br>• በተቋም እና በሀገር አቀፍ ደረጃ ምርት ለማሻሻል ቴክኖሎጂን በማላመድ የመጠቀም ፍላጎቱና ቁርጠኝነት ያለው አመራር ስለመኖሩ<br>• በቴክኖሎጂ የታገዘ ምርት ውጤታማነት ቀድሞ በመረዳት በመተግበር የተገልጋዩና የህብረተሰቡን አስተሳሰብ መቀየር የሚችል መሆኑ እና በተግባርም ያከናወነ<br>• በጥናት በታገዘ መልኩ ተቋሙን ውጤታማ ሊያደርጉ የሚችለሉ የአሰራር መሳሪያዎች ስለመተግበራቸው (ካይዘን፣ አጠቃላይ የጥራት አመራር.....)<br>• በተቋም ደረጃ ተጨባጭ የሆነናቀጣይነት ያለው የመማር እና የማደግ ባህል ማዳበሩ<br>• በሀገር ወይም አለም አቀፍ ደረጃ ከምርትና አገልግሎት አሰጣጥ ጋር ተያይዞ ባመዘገበው የላቀ ውጤት የተገኘ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ወይም ዕውቅና<br>• በተቋሙ ለአዳዲስ የፈጠራና የምርምር ስራዎች ለመስራት የሚያስችል አደረጃጀት ስለመኖሩ | 15 | |
| 5. | የቴክኖሎጂ ሽግግሩና የማሻሻል ሂደቱ ተደራሽነት /ስርጭት<br>• ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ የተሻሻለው የአሰራር ወይም የምርት ሂደት በተቋሙ ያለው ሽፋን<br>• የቴክኖሎጂ ሽግግር በምርት ሂደቱ ተግባራዊ ከሆነ በኋላ በተቋሙ ያመጣው ኢኮኖሚያዊ እና ቴክኖሎጂያዊ እድገት በንፅፅር<br>• በቴክኖሎጂ ሽግግሩ የመጣውን ለውጥ በተለያዩ የሚዲያ ውጤቶች ከማስተዋወቅና ተደራሽ ከማድረግ አንፃር | 10 | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 6. | የቴክኖሎጂ ሽግግር ሂደቱን እንዲፋጠን አስቻይ ሁኔታዎች ስለመኖራቸው<br><br>• ለሂደቱ ተፈፃሚነትና ቀጣይነት ደጋፊ የሆኑ የሳይንስ መሰረተ ልማቶች ስለመኖራቸው<br>• ተግባራዊ የተደረገው ቴክኖሎጂ ቀጣይነት የተሟላ ለማድረግ ሂደቱን በሚደግፍ የሰለጠነ የሰው ኃይል የተደራጀ ስለመሆኑ<br>• የህብረተሰቡ ተቀባይነት ለማግኘት ቴክኖሎጂውን ከማስተዋወቅና የውጤቱ ተጠቃሚ እንዲሆን ከማድረግ አንፃር | 10 | |